# የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ



ግንቦት 2007

# የስታንዳርዱ ዋና ይዘቶች

1. ዳራና አስፈላጊነት
2. የት/ቤት ሱፐርቫይዘሮች የሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ ትኩረት
3. የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ አደረጃጀት
4. የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች
5. የሱፐርቫይዘሮች የሙያዊ እድገት ደረጃዎችና ችሎታዎች
6. የክንውን አመላካቾች

8.የመረጃ አጠነቃቀር መምሪያ /Evidence Guide

# 1.ዳራና አስፈላጊነት

- የሱፐርቫይዘሮች የሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ የማዘጋጀቱ መሠረተ ሃሳብ ዋነኛ ዓላማ በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ስታንዳርድን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ሊያልፉባቸው የሚገባ የሙያዊ እድገት ሥርዓት መፍጠር ነው።
- በሌላ በኩል ደግሞ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ስታንዳርዱን መረዳትና መተግበር ብሎም በስታንዳርዱ መሠረት የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ ብቃት ማሟላታቸውን በምዘና በማረጋገጥ የሙያ ፈቃድ እንዲያገኙ ማስቻል ነው።
- የዚህ ሰነድ ጥቅል ዓላማ ለሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ደረጃ መወሰን ነው።

# የቀጠለ…

- የስታንዳርድ ዝግጅት ጠቀሜታ በአብዛኛው መሠረት የሌለውን የትምህርት ቤት ሱፐርቫዘሮች ምልመላን፣ ሥልጠናን፣ ምረቃን፣ ቅጥርንና ምደባን መከላከል ነው፡፡
- ያለምንም የትምህርትና ሥልጠና ድጋፍ የትምህር ቤት ሱፐርቫይዘሮች በሙያዊ የድጋፍ አሰጣጥ ክንውናቸው ውጤታማነትንና ስኬታማነትን እንዲያሳዩ የመጠበቅ ሁኔታን ለማስወገድም አስተዋጽኦ ያደረጋል፡፡
- ከሁሉም በላይ ግን የስታንዳርድ አቀራረብ የታለመው ቁልፍ የሙያዊ ብቃት ክፍተቶችን በምዘና ለመለየትና የተለየውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን በመቀየስ ሱፐርቫይዘሮቹ ክፍተቶቻቸውን በመሙላት ብቁ ሆነው በሙያቸው እንዲቆዩ ለማገዝ ነው፡፡

# ጽብረቃ/Reflection

1.የትምህርት ቤት ሱፐርቪዥን ጠቀሜታ ?

2.ለአንድ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘር የተሰጡ ተልዕኮዎች/ሃላፊነቶች ወይም ተግባራት ምንድናቸው?10 ያህሉን  ዋና ተግባራትን ለዩ

3.በመቀጠል  እያንዳንዱ ተግባር በግምት የሚወስደውን ጊዜ በፐርሰንት ያስቀምጡ

**4.የት/ቤት ሱፐርቫይዘሮች የአሰራር ችግሮችን ለዩ**

## 2.የት/ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ ትኩረት

ይህ የሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ **የተዘጋጀው**

- **በትምህርት ቤቶችና በክላስተር** ትምህርት ቤቶች ዙሪያ
- ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ እንዲሰጡ
- **በወረዳ/ዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ለተደራጁ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ብቻ ነው።**

- ስታንዳርዱ ለሚከተሉት የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ዋና ዋና የሃላፊነትና የተጠያቂነት ገጽታዎች ትኩረት ይሰጣል።
- ሀ) ተማሪዎች ስኬታማ ዜጋ እንዲሆኑ ለትምህርታቸው ዋጋ በመስጠት እንዲማሩ በቁርጠኝነት መሥራት
- ለ) የመማር ማስተማር ሂደትን የትምህርት ቤቶች ተግባራት ማዕከል አድርጎ ማስቀመጥ
- ሐ) የትምህርት ቤቶችና የማህበረሰቡ ትብብር ለትምህርት ቤቶች አመራርና ተማሪዎች ስኬት ጠቃሚ ነው የሚለውን እውነት መረዳት

# 3. የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ አደረጃጀት

- የሱፐርቫይዘሮች ስታንዳርድ **6** የሙያዊ ብቃት ስታንደርዶችን እንዲያካትት ሆኖ ተዘጋጅቷል።
- እነዚህ **6** የሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች ለትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ከሚያስፈልጉ **አራት ሙያዊ ርዕስ ጉዳዮች** የመነጩ ናቸው። **እነዚህም፡-**

❖ ራዕይና እሴቶች

❖ የግል ባህሪያት ዓይነትና ማህበራዊና የግንኙነት ክህሎቶች

❖ ሙያዊ እውቀትና ግንዛቤ እና

❖ ሙያዊ የተግባራት ክንውን ናቸው።

# የቀጠለ…

- ከስታንዳርዶች አኳያ የተወሰኑ ሙያዊ ተግባራትን የሚያሳዩና እያንዳንዱን ስታንዳርድ የተገነቡ 26 የሚሆኑ ንዑሳን  ስታንዳርዶች ተካተዋል።
- የተወሰኑ የክንውን ደረጃዎችን ለመመዘን እንዲቻል የሚፈለጉ ባህሪያትንና ክንውኖችን ለማየት የሚያስችሉ 141 አመላካቾችም ተለይተዋል።

[ከሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ አኳያ የስታንዳርድ ፩.pptx]

# 4. የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች

**ስታንዳርድ 1፡-** በሙያዊ ተግባራት ክንውን ሂደት ለሕይወት ሙሉ ትምህርት አርአያ ሆኖ ማነቃቃት፣

**ስታንዳርድ 2፡-** ለትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ትምህርት ቤቶችን ማነሳሳት፣ ማካሄድና መምራት

**ስታንዳርድ 3፡-** በትምህርታዊ ተግባራት ክንውኖች ሂደት ወቅታዊ እውቀትንና ግንዛቤን ሥራ ላይ ማዋል።

**ስታንዳርድ 4፡-** ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደርን መተግበር

**ስታንዳርድ 5፡-** በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ አስፈላጊ ሁኔታዎችን መለየትና መተርጎም

**ስታንዳርድ 6፡-** ራስን፣ ግለሰብንና ቡድንን መገንባት

## ስታንዳርድ 1፦ በሙያዊ ተግባራት ክንውን ሂደት በመማር ለሕይወት ሙሉ ትምህርት አርአያ ሆኖ ማነቃቃት

ይህ ስታንዳርድ የመማር-ማስተማር ጥራትንና በትምህርት ቤት የሚሰጠውን ትምህርት ለማሻሻል የሚያስችል ሙያዊ አመራር ለመስጠት የሚያስፈልጉ **እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይገልጻል።**

**ንዑሳን ስታንዳርዶች፦**

- ✓መማርን የስትራቴጂክ እቅድ ማዕከል አድርጎ ማስቀመጥ፣
- ✓ከፍተኛ ስታንዳርዶችን ማስቀመጥ፤
- ✓ በትምህርት ቤት በመማር ስትራቴጂ ዝግጅት ሂደት የአመራር ድጋፍ መስጠት፣
- ✓በትምህርት ቤት የመማር ስትራቴጂ ትግበራን ማረጋገጥ፣
- ✓በትምህርት ቤት መማርና እድገትን መገምገም

# ስታንዳርድ 2፡- ለትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ትምህርት ቤቶችን ማነሳሳት፣ ማካሄድና መምራት

ስታንዳርዱ በትምህርት ቤት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ በስትራቴጂክ ክንውኖችና ውጤቶች ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ለማሳደርና የጥናትና ምርምር ተግባራትን ለማበረታታት በማቀድ በመተግበርና ሪፖርት በማድረግ ግንዛቤን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይገልጻል።

**ንዑሳን ስታንዳርዶች፡-**

- ✓ትምህርታዊ የጥናትና ምርምር ስትራቴጂን በማዘጋጀት የትምህርት ቤት መምህራንንና ርዕሰ መምህራንን ማነሳሳት፣ መደገፍና መምራት፣
- ✓ የትምህርት ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን የተለያዩ የጥናትና ምርምር ቴኪኒኮችን በመምረጥ ለመጠቀም እንዲችሉ መደገፍ፣
- ✓የትምህርት ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን መረጃን በመመርመር ግኝቶችን ለማቅረብ እንዲችሉ መደገፍ፤

## ስታንዳርድ 3፡- በትምህርታዊ ተግባራት ክንውኖች ሂደት ወቅታዊ እውቀትንና ግንዛቤን ጥቅም ላይ ማዋል

ይህ ስታንዳርድ በመማር-ማስተማር **ተግባራት ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ቁጥጥር ሂደት የአመራርና የአስተዳደር ጽንሰ ሃሳቦችንና አሠራሮችን ጥቅም ላይ ለማዋል** የሚያስፈልጉ እውቀት፣ ክህሎትና የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይገልጻል።

**ንዑሳን ስታንዳርዶች፡-**

- ✓ ትምህርት ቤቶች የመማር ተግባራት ክንውኖችን እንዲያሻሽሉ ለመደገፍ የወቅቱን የትምህርታዊ ተግባራት **ክንውኖችን መገምገም፤**
- ✓ ትምህርት ቤቶች **የተሻሻሉ የመማር ክንውኖችን** በመቀበል፣ በማስማማትና የራሳቸውን አደረጃጀቶችና አሠራሮችን በመቀየስ እንዲተገብሩ ማስቻል፣
- ✓ **ውጤታማ** የትምህርት ቤት አገልግሎቶችን በማበረታታት መምራት፣
- ✓ ለትምህርት ቤቶች መሻሻል **ተገቢ ግብረመልሶችንና ድጋፎችን ለመስጠት** የክትትልና ግምገማ ፕሮግራምን በማቀድ ማዘጋጀት፣

# ስታንዳርድ 4፡- ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደርን መተግበር

ስታንዳርድ አራት ውጤታማና አሳታፊ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳርን በማረጋገጥ ለመተግበር የሚያስችሉ **እውቀት፣ ክህሎትና** የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይመለከታል።

ንዑሳን ስታንዳርዶች፡-

- ✓ ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት አመራር ለማረጋገጥ **ለመምህራን ድጋፍ** መስጠት፣
- ✓ **ውጤታማና አሳታፊ** የትምህርት ቤት አስተዳደርን ማረጋገጥ፣
- ✓ ተገቢ **የተማሪዎች ልዩነቶች** አስተዳደርና አያያዝ ሥርዓት እንዲኖራቸው ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ መስጠት፣
- ✓ በለውጥ አስተዳደርና አያያዝ **የስትራቴጂያዊ ለውጥ አስፈላጊነትን**ና ስለውጡ ያሉ እድሎችን በሚመለከት ሃሳቦችን ወይም አስተያየቶችን መስጠት፣
- ✓ **መሻሻልን፣ ፈጠራንና ለውጥን** መምራት፤

# ስታንዳርድ 5፡- በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ አስፈላጊ ሁኔታዎችን መለየትና መተርጎም

ይህ ስታንዳርድ የትምህርት ቤቶች ሥራና የአሠራር ስፋትን ወይም መጠንን ግልጽ ለማድረግ፣ ከውስጥና ከውጪ በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ የተለያዩ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን ለመለየትና ለመተርጎም የሚያስችሉ **እውቀት፣ ክህሎትና** የሚጠበቁ የክንውን ውጤቶችን ይመለከታል፡፡

**ንዑሳን ስታንዳርዶች፡-**

- ✓የትምህርት ቤት ሥራና አሠራር ስፋትን ወይም መጠንን ግልጽ ማድረግ
- ✓ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን መለየት፣
- ✓የተለዩ ትምህርት ቤቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን **መተርጎም፣ መፈተሽና ቅደም ተከተል** ማስያዝ
- ✓በትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገቡ ሁኔታዎችን በመመዝገብ **በሰነድነት መያዝ**፣

# ስታንዳርድ 6፡- ራስን፣ ግለሰብንና ቡድንን መገንባት

ይህ ስታንዳርድ የግለሰብንና የቡድን አቅም ግንበታ ፍላጎቶችን በመለየት ሥራና መማር በሚጣመርበት ቦታ የመማሪያ አካባቢ እድገትን ለማበረታታትና ለመደገፍ የሚያስፈልጉ **እውቀት፣ ክህሎትና** የሚጠበቁ የከንውን ውጤቶችን ይገልጻል፡፡

**ንዑሳን ስታንዳርዶች፡-**

- ✓ የግለሰብና የቡድን የመማርና እድገት ፍላጎቶችን መለየት፣
- ✓ ግቦችን በማስቀመጥ ለራስና ለሌሎች እድገት ሃላፊነት መውሰድ፣
- ✓ ለራስ፣ ለግለሰቦችና ለቡድን ለሙያዊ ትምህርት **እድሎችን መፍጠር**
- ✓ ለራስ፣ ለግለሰቦችና ለቡድን ሙያዊ ትምህርትን በማመቻቸት **ማበረታታት**
- ✓ በመከታተልና በመገምገም የመማር ውጤታማነትን ማሻሻል፡፡

# 6.የክንውን አመላካቾች/Indicators

- የክንውን አመላካቾች በየእያንዳንዱ ሙያዊ ደረጃ ውይም ስታንዳርድ የሱፐርቪዥን ድጋፍ የጥራት ይዘቶችን ወይም ክፍሎችን ይለያሉ።
- ያላቸውን ዕውቀትና ክህሎት ማየትና መለካት የሚያስችል ገላጭ ሀሳቦች ሆነው በምዘና መሣሪያነት ያገለግላሉ።
- አመልካቾች ምን እንደሚመዝኑና ተፈላጊ የክንውን ደረጃዎችን ያመለክታሉ።
- እያንዳንዱ አመልካች የክንውን ውጤትና ደረጃዎችን ሲይዝ በአንድ ንዑስ የሙያ ብቃት ስታንዳርድ ሥር በርካታ አመልካቾች ይገኛሉ።

Supervisors Indicators.docx ..\Supervisors 3.docx
Supervisors4.docx

# የቡድን የተግባር ልምምድ - አንድ

1.በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ/Context/ በት/ቤት ሱፐርቫይዘሮች ስታንዳርድ ውስጥ ከተገለፁት ዋና ዋና ተግባራት በባሕሪያቸው ውስብስብና ለትግበራ አስቸጋሪ/Challenging/ የሚመስሉ ንዑስ ስታንዳርዶች/Elements/ ወይም አመላካቾችን /Indicators/ ለዩ

2.እነዚህን የተለዩ ተግባራትን ለማከናወን አስቸጋሪ የሚያደርጓቸውን ምክንያቶች በተጨባጭ ፈታ አድርገው ያቅርቡ

# 5. የሱፐርቫይዘሮች የሙያዊ እድገት ደረጃዎችና ችሎታዎች

- በትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርድ ውስጥ አራቱ የሙያዊ እድገት ደረጃዎች በሙያዊ ተግባራት ክንውን ሂደት ስታንዳርዶቹን ላሟሉና ችሎታውን ላላቸው ሱፐርቫይዘሮች እው ቅናን ለማመልከት የሚሰጡ የሙ ያ እድገት ደረጃዎች ናቸው፡፡
- በደረጃዎቹ ውስጥ ማለፍ ከግንዛቤና እውቀት፣ ከንድፈ ሃሳቦችና ልምዶች /ተሞክሮና ክህሎት መጨመር፣እንዲሁም ከውስብስብ ሙያዊ በሕሪያትና ሥነምግባር ማሻሻል ጋር ተዛማጅነት አላቸው፡፡
  - ✓ ጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች /**Beginner Supervisors**
  - ✓ ብቁ 1 ሱፐርቫይዘሮች /**Proficient-1 Supervisors**
  - ✓ ብቁ 2 ሱፐርቫይዘሮች /**Proficient- 2 Supervisors**
  - ✓ መሪ ሱፐርቫይዘሮች /**Lead Supervisors**

  CHART.pptx

# 5.1. ጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች

- ጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች በመምህርነት፣ በትምህርት ክፍል ሃላፊነት፣ በዩኒት መሪነትና ወይም በትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርነት በመሥራት የትምህርት ቤት ልምድና ተሞክሮ እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል።
- በትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘርነት የሚፈለግባቸውን የመነሻ ትምህርትና ሥልጠና በመውሰድ የሚጠበቅባቸውን አካዳሚክ ደረጃ ማሟላትም ይኖርባቸዋል።
- በትምህርት ቤቶች የመማር-ማስተማር ሂደትን ለመከታተል የሚያስችል መሠረታዊ እውቀትና ክህሎት ይኖራቸዋል።

# የቀጠለ…

- የትምህርት ቤት ውጤቶችን ለማሻሻል የሙያዊ አመራር ሚናቸውንና ሃላፊነታቸውን እንደዚሁም ወቅታዊና ተገቢ ግብረመልሶችን እንዴት መርጠው መስጠት እንዳለባቸውም ይረዳሉ፡፡
- ለትምህርት ቤቶች መሻሻል በስተራቴጂክ እቅዶች ዝግጅትና ትግበራ ትምህርት ቤቶችን መደገፍ ይችላሉ፡፡
- በተገቢ ሥነምግባርና በቅንጅት ከሥራ ባልደረቦችና ከትምህርት ቤት ማህበረብ ጋር የመሥራት ጠቀሜታን ይረዳሉ፡፡

## 5.2 ብቁ 1 ሱፐርቫይዘሮች

- ከጀማሪ ሱፐርቫይዘሮች የሚጠበቀውን ሁሉ ከማሟላት በተጨማሪ ብቁ 1 ሱፐርቫይዘሮች ለትምህርት ቤት መምህራንና ርዕሰ መምህራን ውጤታማ ድጋፎችን መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። ፍላጎቶችን በመመዘን ድጋፎቻቸውን ከፍላጎቶቹ ጋር ማስማማት መቻል አለባቸው።
- ከሥራ ባልደረቦች ጋር በቅንጅት መሥራት ይችላሉ፤ በሙያዊ ክንውናቸው ላይ ተፅዕኖ በሚያሳድሩ ትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ምክር ወይም ድጋፍ ለመስጠት ይጥራሉ።

# የቀጠለ…

- በሁሉም <u>የምክክር መድረኮች</u> በተገቢ ሙያዊ ሥነ ምግባር ይሳተፋሉ። እነዚህ ሱፐርቫይዘሮች እውቀት ያላቸውና ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚሠሩ ባለሙያዎች <u>ንቁ አባላት ናቸው።</u>
- ለሥራ ባልደረቦቻቸው <u>ትምህርታዊ አስተዋጽኦ</u> ለማድረግ ችሎታውንና ክህሎቱን አላቸው። <u>ሌሎችን የመምከርና የመምራት ሚና መጫወትም</u> ይችላሉ።
- አዎንታዊና ምርታማ የመማሪያ አካባቢን ለመፍጠር መምህራንን ጨምሮ ለሥራ ባልደረቦችና ለርዕሰ መምህራን <u>ስትራቴጂዎችን በማበርከት</u> ይደግፋሉ።

# 5.3 ብቁ 2 ሱፐርቫይዘሮች

- ከላይ ከተጠቀሱት ሁለቱ ደረጃዎች የሚጠበቁትን ጨምሮ

  በብቁ 2 ደረጃ ላይ ያሉ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በሙያዊ ደረጃቸው የትምህርት ቤት ሱፐርቭዥን <u>ንድፈ ሃሳቦችንና ልምዶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ጥልቅ እውቀትና ሊታይ የሚችል ክህሎት</u> እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል።

- በትምህርት ቤት ማህበረሰብ እንደዚሁም በትምህርት ቤቶች፣ በወላጆችና በሰፊው ህብረተሰብ <u>መካከል ስኬታማና ውጤታማ የቡድን ሥራ ባህልና መንፈስን</u> መፍጠር ይኖርባቸዋል።

# የቀጠለ…

- የፖሊሲ፤ የስትራቴጂዎችና የፕሮግራሞች ትግበራን በማመቻቸት ትልቁን ሚና መጫወትም አለባቸው፡፡
- በደረጃቸው በሱፐርቪዥን ተግባራት ከነውን አርአያ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
- በትምህርት አዳዲስ የእድገት ውጤቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ፡፡ በትምህርት ቤቶች የመማር-ማስተማር ሂደትን ለማሻሻል የትምህርት ቤቶች የምዘና መረጃን በመፈተሽ ይጠቀማሉ፡፡
- ለሥራ ባልደረቦች ሙያዊ ትምህርትንና የልምድ ልውውጥ እድሎችን ከፍ የሚያደርግ አካባቢን ለመምሥረት ወይም ለመፍጠርም ንቁ ናቸው፡፡

# 5.4 መሪ ሱፐርቫይዘሮች

- ከላይ በተገለፁ 3 ደረጃዎች ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው መሪ ሱፐርቫይዘሮች የተከበሩና በከፍተኛ ደረጃ እውቅና ያገኙ ባለሙያዎች ናቸው።
- ከሥራ ባልደረቦች፣ ከትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ ከመምህራን ከወላጆች፣ ከትምህርት ቤት ማህበረሰብና ከህብረተሰቡ ጋር አክብሮት የተሞላበትና ውጤታማ የሆኑ ተግባቦቶችን ፈጥሮአል።
- ሁልጊዜ በፈጠራ የታጀበ አስተማማኝ የአመራር ተግባራት ክንውኖችን ማሳየት ይችላሉ።
- ለመማር ልዩነቶች ዋጋ በመስጠትና በማክበር የተለያዩ ተማሪዎች ፍላጎቶችን ማርካት የሚችል አካባቢን ለመፍጠር በቀርጠኝነት ይሠራሉ።

# የቀጠለ…

- በትምህርት ቤቶችና በቁልፍ ባለድርሻዎች መካካል ስኬታማና ውጤታማ የአጋርነት ሥርዓት በመፍጠር፣ የፕሮግራሞችን ዘላቂነት የሚያረጋግጡ ስትራቴጂዎችን ያስተዋውቃሉ፣
- ከፖሊሲና ስትራተጂዎች ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ተግባራት ላይ ሥልጠናዎችን በመስጠት፣
- የፕሮግራሞች ትግበራ ያስገኛቸው ውጤቶችን አስመልክቶ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳሉ።
- በዚህ ደረጃ ያሉ የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በማህበረሰቡ ውስጥ ትምህርት ቤቱንና የማስተማር ሙያውን ይወክላሉ።

# 7.የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶች ማረጋገጫ መምሪያ (Evidence Guide)

**7.1 የምዘናውን ሂደት ለማካሄድ የሚያገለግሉ መረጃዎች፤**

**7.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፤**

**7.3 የመረጃ ምንጭ፤**

**7.4 ምዘናው የሚካሄድበትን ቦታ በግልጽ ያመለክታል።**

Supervisors  evidence guide.docx

Performance Criteria.docx-5.docx

# አመሰግናለሁ